የጥቃት ጥበቃ ጉዳዮች ሞጁል 2

የጥቃት ጥበቃ፡- ከአጋሮች ጋር መጀመር

በጥቃት ጥበቃ ላይ ከሚሰጠው ባለአምስት ክፍል የበይነ-መረብ ተከታታይ ትምህርት ውስጥ ይህ ሁለተኛው ሞጁል ነው፡፡ ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተገናኙ ተጨባጭ ጉዳዮች ላይ የሚሠራ ፋሚሊ ሄልዝ ፍሮንቲየርስ (ኤፍ. ኤች. ኤፍ) የተባለ ምናባዊ ብሔራዊ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅትን ታሪክ መሠረት በማድረግ ተከታታይ ትምህርቱ ከጥቃት ጥበቃ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ፅንሰ-ሃሳቦችን ያስተዋውቃል።

መግቢያ

ለገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ፕሮፖዛሎችን መጻፍ

የፕሮግራም ምስረታ

የተቋማዊ የአሠራር ባህል

ማጠቃለያ

መግቢያ

ወደ ሞጁል 2 እንኳን በደህና ተሸጋገሩ

በዚህ ክፍል ውስጥ የኤፍ. ኤች. ኤፍ ቡድን በጥቃት ጥበቃ ላይ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር አብረው ይቀጥላሉ::

በሚከተሉት ውስጥ የጥቃት ጥበቃ በምን ሁኔታ ሽፋን እንዳገኘ ሞጁሉ ያብራራል፡-

- ለገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ፕሮፖዛል መፃፍ፤
- ደህንነቱ የተጠበቀ ፕሮግራም ማቋቋም፤ እና
- ተቋማዊ የአሠራር ባህል።

የጥናት ጊዜ ፡- 1 ሰዓት

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህ ሞጁል የሚከተሉትን ለማድረግ ይረዳዎታል፡-

- ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የተገቢ ጥንቃቄ ግምገማ (due diligence) ለተቋማትና ለአጋር ድርጅቶች የሚኖረን ፋይዳ ለመረዳት፤
- ደህንነቱ የተጠበቀ ፕሮግራም ለመንደፍ/ለመቅረጽ የሚያስችሉ ቁልፍ የሆኑ ከጥቃት ጥበቃ ተግባራትን በፕሮግራም ዑደትውስጥ ለመለየት፤ እና
- ደህንነቱ ወደተጠበቀ አሠራር ለመሸጋገር ጠንካራ የሆነ የአመራር ሰጭነት እና የተቋማዊ/ድርጅታዊ አሠራር ባህል አስፈላጊነትን ለመገንዘብ::

ሞጁሉ 3 ክፍሎች አሉት፡-

ክፍል 1፡- የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ፕሮፖዛል መፃፍ

ስለ ጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች፣ የዝግጅት ማረጋገጫ ሂደቶች፣ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ ማዕቀፎች እንዲሁም ኤፍ.ኤች.ኤፍ ከታች እርከን (በማኅበረሰቡ ውስጥ) ፕሮጀክቶቹን የሚተገብሩ አጋሮቹን ፍላጎት እንዴት ግምት ውስጥ ማስገባት እንደጀመረ ለማወቅ ይሞክሩ::

ክፍል ሁለት - የፕሮግራም ዝርጋታ

ደህንነቱ ከተጠበቀ የፕሮግራም ዝግጅት እና በአዲስ ፕሮግራም ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ ደረጃዎች እንዲሁም ከኤፍ.ኤች.ኤፍ የጨቅላ ሕጻናት ከትባት ፕሮግራም ጋር የጥቃት ጥበቃን በምን ሁኔታ ማስተሳሰር እንደሚቻል ይፈትሹ:: በተጨማሪም ከጥቃት ጥበቃ እና በሥራ ቦታ ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም ማለት ምን እንደሆነ ይተዋወቃሉ::

ክፍል 3 - ተቋማዊ የአሠራር ባህል

የኤፍ.ኤች.ኤፍ ተቋማዊ የአሠራር ባህል እና አመራር መለየት፤ የጥቃት ጥበቃ መስፈርቶች ተጠያቂነትን፣ ክትትልን እና ሙያዊ አተገባበርን እንዴት ለመቆጣጠር እንደሚያስችሉና የተቋም አመራሮች ለጥቃት ጥበቃ ስለሚወስዱት ኃላፊነት ጠቀሜታ መመልከት፡፡

ስለ ኤፍ.ኤች.ኤፍ ተቋም ፣ አጠቃላይ ሁኔታ እና
ቡድን ማስታወስ ከፈለጉ፦

አጠቃላይ ሁኔታ/ዓውድ

ፋሚሊ ሄልዝ ፍሮንቲየርስ (ኤፍ.ኤች.ኤፍ) የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ላይ ትኩረት በማድረግ የሚንቀሳቀስ መካከለኛ ደረጃ የሲቪል ማኅበረሰብ ተቋም ነው፡፡

ኤፍ.ኤች.ኤፍ የሚገኘው/የሚንቀሳቀሰው ጉልህ የሆነ የደህንነት ስጋት ባለበት አገር ነው። አገሪቱ ድህነት የተንሰራፋባት እና በአብዛኛው የገጠሩ ክፍል ደካማ የትምህርት ተደራሽነትና የመጀመርያ ደረጃ የጤና አጠባበቅ አገልግሎት የሚገኝባት ናት። ያሉት የሕግ ማዕቀፎች ግለሰቦችን ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ለመከላከል የማያስችሉና ደካማ ናቸው፡፡ በሥራ ላይ ያሉት ሕጎችም በደንብ የማይተገበሩና በቀላሉ ሊጣሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

ቡድኑ

ኤፍ.ኤች.ኤፍ 25 የአገር ውስጥ ሠራተኞች አሉት። የድርጅቱ መዋቅር የቡድን አመራረጡን ያሳያል፤ በተለይም የጥቃት ጥበቃ ኃላፊነት ያላቸውን።



ለገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ፕሮፖዛሎችን መጻፍ

የገንዘብ ድጋፍ ለመጠየቅ የሚረዳ ፕሮጀክት ማዘጋጀት

ለፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ገንዘብ ለማግኘት ኤፍ.ኤች.ኤፍ አብዛኛውን ጊዜ ፕሮፖዛሎችን ይጽፋል። የስኬት ዕድሉን ከፍ ለማድረግ የዚህ ሂደት አካል የሆኑ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያከናውናል።

የተጠቃሚዎችንና የሠራተኞችን ደህንነት ለማረጋገጥ ኤፍ.ኤች.ኤፍ በፕሮግራም እና ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች ውስጥ የጥቃት ጥበቃ ጉዳዮችን እንደዋና መስፈርት ማካተት ይኖርበታል። ይህም በተጨማሪ ለጥቃት ጥበቃ ያላቸውን ቁርጠኝነት በሚመለከት ለለጋሾችና ገንዘብ ሰጭዎች ጠቃሚ መልዕክት ያስተላልፋል።

ክፍል ፣ ስለ ጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች፣ ስለ ቅድመ ዝግጅት ማረጋገጫ ሂደቶች፣ ስለ ጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ ማዕቀፍ እንዲሁም አጋሮቹ ደህንነቱ የተጠበቀ ሥራ ለማከናወን ምን እንደሚፈልጉ የኤፍ.ኤች.ኤፍ ቡድን እንዴት ምላሽ መስጠት እንደጀመረ ያስተዋውቃል።

ከከፍተኛ የጨቅላ ሕፃናት ሞት ጋር ተያያዥነት ላለው የጨቅላ ሕፃናት የጤና ክትባት ፕሮግራም የሚውል ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮፖዛል እንዲያስገባ ኤፍ.ኤች.ኤፍ ተጋብዟል። የገንዘብ ድጋፉ የተሰጠው በአንድ ዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅት ነው።

ዋና ጉዳይ አስፈጻሚ ሆና የተሾመችው ዝናሽ ሀፍቶም በለጋሽ ድርጅቶች በኩል በጣም የታወቀችና የተከበረች ናት፣ በዚህም ምክንያት ነው ኤፍ.ኤች.ኤፍ ፕሮፖዛል እንዲያቀርብ የተጋበዘው።

የኤፍ.ኤች.ኤፍ የገንዘብ ማሰባሰብ እና የፕሮግራም ቡድኖች በጨቅላ ሕፃናት የጤና ክትባት ፕሮግራም ፕሮፖዛል ላይ በጋራ መሥራት ጀምረዋል። በቅድመ ጥንቃቄ ግምገማ ሂደት የጥቃት ጥበቃ ክፍልን ማጠናቀቅ እንደሚገባቸው በቅርቡ ተገንዝበዋል። ኤፍ.ኤች.ኤፍ ከዚህ በፊት ይህን ሠርቶ አያውቅም፣ ይህም ፕሮፖዛላቸውን ደካማ እንዳያደርገው የቡድኑ አባላት ስጋት አላቸው።

ያስታውሱ፦

የተገቢ ጥንቃቄ ግምገማ (due diligence) አንድ ተቋም አንድን ፕሮግራም ለመፈጸም የሚያስችል አቅም መኖሩን ለመገምገም የሚደረግ ማስረጃ የማሰባሰብ ሥራ ነው። የጥቃት ጥበቃን በተመለከተ የሚደረግ የተቋም አቅም ግምገማ ለጋሽ ድርጅቶች ከተቋማት የሚጠብቋቸውን ደረጃዎች ወይም ቅድመ ሁኔታዎች ለምሳሌ ተቋሙ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ አለው ወይስ የለውም የሚሉትን ያካትታል።

የኤፍ.ኤች.ኤፍ ፕሮግራም ቡድን የተቋማዊ አቅም ግምገማ አካል የሆነውን የጥቃት ጥበቃ ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ማስረጃ የማሰባሰብ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። ይህ በባለፈው ዓመት በተሰጠው ዓመታዊ የጥቃት ጥበቃ ሥልጠና ወቅት ያልተሸፈነ በመሆኑ ምን ዓይነት መረጃ እንደሚያስፈልግ ቡድኑ እርግጠኛ አይደለም። የፕሮግራሙ ማኔጀር የሆነው አህመድ መሐመድ፣ ይህን ሥራ እንድትመራ ከፕሮግራም አፈሠሮች መካከል አንዷ የሆነችውን አስቴር ዘማችን ጠይቋታል።

"አዲሷን ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዝናሽን ለማስደሰት ይህ በእርግጥ ጥሩ አጋጣሚ ነው። አስቴር ውስጣዊ ብቃቷን ታውቃለች ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።"



"ይህ በዕርግጥ አጓጊ ይመስላል፣ ነገር ግን ከፍተኛ ስጋት ያለው ፕሮጀክት ሊሆን ስለሚችል በትክክል መሥራት ይጠበቅብናል። በቦታው ሊኖር ስለሚገባው ጉዳይ ከዚነት ሙህባ ጋር መነጋገር አለብኝ።"



"የኤፍ.ኤች.ኤፍ የጥቃት ጥበቃ የመተግበር አቅምን በተመለከተ ማስረጃዎችን ለመለየት ምን ሊረዳን ይችላል?

"የተቋም አቅም ግምገማ የዓለም አቀፍ መስፈርቶችን መሠረት ያደረገ መሆኑን አውቃለሁ ነገር ግን እነዚህ መስፈርቶች የተለያየ ይዘት ስለሚኖራቸው የትኩረት አቅጣጫዎችም የተለያዩ ናቸው። እኔ እንደማስበው ዚነት ለኤፍ.ኤች.ኤፍ በሚጠቅም መልኩ የማላመድ/ የማጣጣም ሥራ ሠርታ ሊሆን ይችላል። በዚህ ጉዳይ ላይ የበለጠ ጥናት ማድረግ ይኖርብኛል።"

የጥቃት ጥበቃ ጉዳይ ዋና ተጠሪ ሆና በዝናሽ ከተወከለች ጀምሮ ዚነት የተወሰኑ ሥeልጠናዎችን ወስዳለች፣ በመሆኑም ባልደረቦቿን ለማማከር የበለጠ በራስ የመተማመን ስሜት ፈጥሮላታል።

ዚነት የተለያዩ የዓለም አቀፍ የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎችን ለአስቴር ታሳያታለች እንዲሁም እያንዳንዳቸዉ መመዘኛዎች የራሳቸው የተለየ ትኩረት እንዳላቸው ትገልጽላታለች።



በዓለም አቀፍ የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ የአገናኝ ድሩን ይጫኑ፡-

ከወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት መከላከል	ሕፃንን ከጥቃት መጠበቅ	ከጥቃት እና ትንኮሳ በሥራ ዓለም ውስጥ	ወሲባዊብዝበዛን፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ
የ2003 የዋና ፀሐፊው ልዩ ዕትም የ2016 የተቋማዊ ጥምረት ቋሚ ኮሚቴ (IASC) የወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት መከላከል (PSEA) ዝቅተኛ የአተገባበር/የአሠራር ደረጃዎች የ2014 መሠረታዊ የሰብዓዊነት መመዘኛ	የ2014 የሕፃናት ደህንነት አጠባበቅ የሕፃናት ጥቃት ጥበቃ መመዘኛወች የሕፃናት ደህንነት አጠባበቅ የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች ማጠቃለያ፡፡	ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ድርጅት ስምምነት 190፣ ምክረ ሃሳብ 206	የኢኮኖሚ ትብብርና የልማት ድርጅት (OECD) የልማት አጋዥ ኮሚቴ (DAC) ወሲባዊ ብዝበዛን፣ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን ለማስቆም ምክረ ሃሳብ በልማት ትብብር እና የሰብዓዊነት ዕርዳታ

ለበለጠ መረጃ፣ ይመልከቱ አጭር ማጠቃለያ፡- ዓለም አቀፍ መመዘኛዎች ስለ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃት እና ትንኮሳ፡፡

ዋና ጥቆማ

ተቋማት የሚያገኟቸውን ሰዎች ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ በደል እና ወሲባዊ ትንኮሳ ለመጠበቅ ሁሉንም ዓይነት ምክንያታዊ እርምጃዎች መውሰድ እንዳለባቸው ለጋሽ ድርጅቶች ታሳቢ ያደርጋሉ፡፡ ይህም ሠራተኞችን እንዲሁም ፕሮግራሞች በሚተገበሩባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎችን ያጠቃልላል፡፡

አብዛኛውን ጊዜ ለጋሽ ድርጅቶች ለማንኛውም ተቋም የድጋፍ ገንዘብ ለመስጠት ከመስማማታቸው በፊት ዋስትና ይፈልጋሉ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ሥጋቶችን በመገምገም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉለት ማንኛውም ድርጅት ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እየተንቀሳቀሰ ስለመሆኑ እና የሰዎችን ደህንነት ማስጠበቅ ስለመቻሉ ማረጋገጥና ደስተኛ መሆን ይፈልጋሉ፡፡

ስለዚህ አንድ ተቋም የገንዘብ ድጋፍ ከማግኘቱ በፊት ዓለም አቀፍ የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎችን መሠረት በማድረግ በጥቃት ጥበቃ ላይ ያለውን አቅም እንዲገመግም ሊጠየቅ ይችላል፡፡ እንዲሁም ደጋፊ ማስረጃዎችን መሰብሰብ እና ማቅረብ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ የገንዘብ ድጋፍ ውሳኔው በመረጃ የተደገፈ እንዲሆን እነዚህ ሰነዶች ምርመራ ሊደረግባቸው ይችላል፡፡

- ✓ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ
- ✓ ሕገወጥ አሠራርን ለማጋለጥ የሚረዳ ፖሊሲ
- ✓ የሥነ ምግባር ደንብ
- ✓ የጥቃት ጥበቃ ዋና ተጠሪ
- ✓ የሪፖርት ማድረጊያ መንገዶች
- ✓ የስጋት ምዝገባ

የዓለም አቀፉ የሰብዓዊነትና የልማት ድርጅቶች ሕብረት የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን የመከላከል አተገባበር የሚረዳ ፈጣን የማጣቀሻ መጽሐፍን መሠረት በማድረግ ዚነት ያሰባሰበቻቸውንና ለኤፍ.ኤች.ኤፍ የሚረዱ የተለያዩ መመዘኛዎችን አስቴር አግኝታቸዋለች፡፡ የጥቃት ጥበቃ አቅም ግምገማ መስፈርቶችን ለማረጋገጥ አስቴር በተለያዩ የተቋሙ የሥራ እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ጀምራለች።

የጥቃት ጥበቃ አቅም ግምገማ መስፈርቶችን ለማሟላት/ለማሳካት አስቴር ምን ዓይነት ማስረጃዎችን መሰብሰብ እንዳለባት አሁን ትማራላችሁ፡፡

ያስታውሱ፡-

የማረጋገጫ መንገዶች የምንላቸው ሁሉም ተግባራት መሟላታቸውን፣ ዓላማዎች እና ውጤቶች መሳካታቸውን እንዲሀም በፕሮጀክቱ የታለሙ ውጤቶች መገኘታቸውን ለማረጋገጥ የምንሰበስባቸው ሰነዶች ናቸው። ለኤፍ.ኤች.ኤፍ፣ የማረጋገጫ መንገድመስፈርቶች የምንላቸው የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች በምን መልኩ እንደተፈጸሙ የሚያሳዩ ሰነዶች ናቸው።

የዓለም አቀፉ የሰብዓዊነትና የልማት ድርጅቶች ሕብረት የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን የመከላከል አተገባበር ፈጣን የማጣቀሻ መጽሐፍ።

1.1 ከኤፍ.ኤች.ኤፍ መደበኛ እንቅስቃሴ ጋር ማመሳከሪያ መንገድ

ለኤፍ.ኤች.ኤፍ የቀረቡትን መመዘኛዎች ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ትክክለኛ መንገዶችን መምረጥ እንዲችል ያግዙ::

ከተመለከቱት የኤፍ ኤች ኤፍ/FHF -ስታንዳርዶች/ደረጃዎች በግራ በኩል ካለው የቁልቁል አመልካች ሥር ከተዘረዘሩት ውስጥ FHF የማረጋገጫ መንገዶችን መምረጥ እንዲችል እገዛ ያድርጉ።

የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ	የጥቃት ጥበቃ ሥልጠና መዛግብት እንደሚያሳዩት ሁሉም ሠራተኞች ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተያያዘ ስለሚጠበቅባቸው ኃላፊነቶች ትምህርት ወስደዋል። የጥቃት ጥበቃ ተጠሪዎች ልዩ ሚናቸውን መረዳት እንዲችሉ የሚያግዝ የተለየ ሥልጠና ያስፈልጋቸዋል።
የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ	ቅሬታ የመቀበያ መዝገቡ የሪፖርት ማድረጊያ መንገዶች በቦታው መኖራቸውን፣ የታወቁ መሆናቸውን፣ ግንዛቤ የተወሰደባቸውና ጥቅም ላይ የዋሉ መሆናቸውን ያሳያል። ቅሬታውን ከሚመረምሩ ሰዎች ውጭ ሌሎች ሰዎች ጉዳዩን እንዲመለከቱት የሚቀርብ ከሆነ የማንነት አመልካች ዝርዝር መረጃዎች እንዳይታወቁ መደበቅ አለባቸው።
የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ	የፕሮግራም ስጋቶች ተለይተው የታወቁ መሆናቸውን እንዲሁም እነዚህን ስጋቶች ለመቀነስ የሚረዱ የመቆጣጠሪያ ዕቅዶች በቦታው መኖራቸውን በሰነድ የተያዙ የስጋት መቆጣጠሪያ ቅጾች ያሳያሉ።
የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ	የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲው፤ የወሲባዊ ብዝበዛን፣ ጥቃትን እና ወሲባዊ ትንኮሳን ለመከላከል የሚረዱ ፖሊሲዎችና አሠራሮች አንደኛው ጠቃሚ ክፍል ሲሆን ተቋሙ ለጥቃት ጥበቃ ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል።
የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ	በሰነድ የተያዙ የጉዳይ (የኬዝ) ምርመራዎች የሚያሳዩት ቅሬታዎች በአግባቡ ምላሽ እንደተሰጣቸው ነው። ስለአንድ ተቋም የጥቃት ጥበቃ አቅም የሚደረግ ግምገማ፣ ከቅሬታ ጉዳይ ጋር የተገናኙ ዝርዝር የምርመራ ሂደቶችን ሊፈትሽ ይችላል። ነገር ግን በጉዳዩ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተሳትፎ ካላቸው ሰዎች ውጭ ሌሎች ሰዎች እንዲመለከቷቸው የማይፈቀዱ እውነተኛ የሆኑ የጉዳይ (የኬዝ) ምርመራዎችን አይመለከትም።
የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ	የሕፃናትን እና የማኅበረሰቡን ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚረዱ ተግባራት እና ቁሳቁሶች፣ ተቋሙ እነሱን ከጥቃት ለመጠበቅ ያለውን ቁርጠኝነት መገንዘብ እንዲችሉ መልካም ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል።
የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ	ራሱን የቻለ ሚና ያለው አንድ ሰው የጥቃት ጥበቃ ዋና ተጠሪ ሆኖ ተመድቧል። ይህ ልዩ የሆነ የሥራ ሚና በጥቃት ጥበቃ የሥራ ውል ስምምነት ሊደገፍ ይገባዋል።

መልሶቹን ለመመልከት፣ **እዚህ ይጫኑ::**

ሌሎች ተጨማሪ የማረጋገጫ መንገዶች አሉ፤ ነገር ግን ይህ መልመጃ በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁ የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ጠንቅቀው እንደተረዱ ያሳያል፡፡

ያስታውሱ! የተለያዩ ሊጋሾች የተለያዩ የተቋም መመዘኛ መስፈርቶችን ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ የሚሠሯቸውን ሥራዎች እንዲሁም ምን ዓይነት ተቋም እንደሆነ የሚያሳዩ መመዘኛዎችን በማዘጋጀት ኤፍ.ኤች.ኤፍ ለዚያ ዝግጁ ለመሆን እየሞከረ ነው፡፡

በኤፍ.ኤች.ኤፍ መመዘኛዎች ውስጥ አንዳንድ የጎደሉ መስፈርቶች እንዳሉ ልብ ብለዋል?
ቀርተዋል ብለው የሚያስቧቸውን መመዘኛዎች በመጻፊያው ሳጥን ውስጥ ይጻፉ።

መልሶቹን ለመመልከት፣ እዚህ ይጫኑ፡፡

የጥቃት ጥበቃ አቅም ግምገማ መስፈርቶችን ለማረጋገጥ አስቴር በተለያዩ የተቋሙ የሥራ እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ ጀምራለች። በበርካታ የጥቃት ጥበቃ መመዘኛ ክፍሎች/ዘርፎች ውስጥ የጥቃት ጥበቃ ማረጋገጫዎችን ለማቅረብ የሚያስችል ተጨባጭ ማስረጃ እንዳላት እርግጠኛ ናት። ማንኛውም የጎደለ ነገር ካለ ደግማ እንድታጣራ አስቴር ለዚነት ነግራታለች። ዚነት በበኩሏ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲዎች በሥጋት ላይ ያሉ ሕፃናትንና አዋቂዎችን ጨምሮ ሁሉም ተጠቃሚዎች እና በተቋሙ ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ላይ ያነጣጠሩ ጉዳቶችና እና በደሎችን መፍታት እንዳለባቸው ለአስትር አስታውሳታለች።



ኤፍ.ኤች.ኤፍ በቂ የሆነ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲዎች እንደሌሉት፣ እና በተቋሙ ውስጥ የሚገኙትም ቢሆኑ መሻሻል የሚገባቸው የተወሰኑ መሠረታዊ ነገሮች ብቻ እንደሆኑ አስቴር ተገንዝባለች።

"አዋቂ ከሆኑ ተጠቃሚዎች ጋር የተያያዘ ሕገወጥ እና አግባብነት የሌለው አሠራርን ከማጋለጥ በዘለለ / ባለፈ ብዙ ፖሊሲዎች ሊኖሩ ይገባል። በተመሳሳይ ሁኔታ አጋሮችን የሚመለከት ምንም ነገር አላየሁም።"

1.2 የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ እና የአሠራር ሂደት እንቅስቃሴ

ከሚከተሉት የተቋማዊ ፖሊሲዎች እና አሠራሮች ዝርዝር ውስጥ ከጥቃት ጥበቃ ጋር በሚጠቅም መልኩ ተያያዥነት ሊኖራቸው የሚችሉትን ይጫኑ።

ፀረ-መድልዎ ☐	የአደጋ ክስተት አያያዝ ☐	ሥርዓተ ፆታ ☐	ቴክኖሎጂ ☐
የሥነ ምግባር ደንብ ☐	ፀረ የጉልበተኝነት ጥቃት ☐	እርምት ☐	የሕጻናት ጥቃት ጥበቃ ☐
የሕጻናት ጥበቃ ☐	ቅሬታዎች ☐	የጥቃት ሰለባ/ከጥቃት በሕይወት የተረፈ ☐	ከወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት መከላከል ☐
ወሲባዊ ትንኮሳ ☐	ምልመላ ☐	ሕገ ወጥነትን/ ያለአግባብ አሠራርን የማጋለጥ አሠራር ☐	መረጃ እና ግንኙነት ☐

መልሶቹን ለመመልከት፣ **እዚህ ይጫኑ።**

ጠቃሚ ምክር፡-

ተቋማት አንዳንድ ጊዜ ጠቃሚ የሆኑ ሁሉንም ዓይነት ፖሊሲዎች የሚያመላክት የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ ማዕቀፍ ያዘጋጃሉ። ይህም የድርጅቱን ራዕይ እና እሴቶች እንዲሁም እነዚህን ለመፈጸም የሚረዱ ዕቅዶችን የሚደግፉ አጠቃላይ መመሪያዎችን በመዘርጋት ሠራተኞች ስለሥራ ቦታቸው የተሻለ አጠቃላይ ዕይታ እንዲኖራቸው ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ ተቋሙ ሊያሰፍን እየጣረ ስላለው የሥራ ባህል ዓይነት ሠራተኞቹ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው፤ ከእነርሱ ምን ዓይነት ባህርይ እንደሚጠበቅ፣ እና እነዚህን ሁሉ እንዴት ማሳካት እንደሚቻል እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል።

አስቴር አጠቃላይ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ ማዕቀፍ እና ለተቋም አቅም ግምገማ የሚረዳ ደጋፊ ማስረጃዎችን ለመፍጠር ችላለች።

አስቴር ከሌላ የፕሮግራም ኦፊሰር ጋር እየተነጋገረች ነው። ለኤፍ.ኤች.ኤፍ ስለሠራችው ሥራ ባልደረባዋ እንኳን ደስ አለሽ በማለት እንዲህ አለቻት፡-

"ሁሉንም የወረቀት ላይ ሥራዎች ወደ አንድ ማምጣት መቻልሽ በጣም የሚያስደንቅ ነው። በጥሩ ሁኔታ ተከናውኗል!"

"አዎ፣ አብዛኞቹ ፖሊሲዎች በመደርደሪያ ላይ ለዓመታት የቆዩ በመሆናቸው ተግዳሮት ሊሆን የሚችለው ወደ ተግባር ለመቀየር ነው"

ያስታውሱ፦

ተቋማት ውጤታማ የሆነ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ እንዲኖራቸው፣ የሠራተኞችን ግንዛቤ በሥልጠና እና ሥርፀት (induction) ማሳደግ፤ እንደ የጥቃት ጥበቃ መሪዎች የመሣሠሉ አስፈላጊ ግብአቶች መኖራቸውን በማረጋገጥ እንዲሁም የሰው ኃይል አስተዳደር እና የሥራ ግንኙነት በመሣሠሉ ተያያዥነት ባላቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ ጠንካራ የሆነ ትብብር በሥራ ክፍሎች መካከል መዘርጋት የመሣሠሉትን ጨምሮ በአተገባበር ሂደት ሁኔታዎችን ቀድሞ ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ቀልጣፋ የአሠራር ሥርዓቶችን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው።

ለበለጠ መረጃ፣ ይመልከቱ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ ምሳሌዎች።



ውድ FHF,

እንኳን ደስ አለዎት FHF ጥንቃቄ የተሞላበት የጥቃት መስፈርቶችን አሟልቶ የህፃናት የክትባት መርሃግብርን ለመተግበር ያቀረበው ማመልከቻ ውጤታማ ሆኗል ::

ከትህትና ጋር፣ የእርስዎ
አንድ ለጋሽ

ግምገማውን በተሳካ ሁኔታ የማጠናቀቃቸውን እና ለጋሾችም የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ የመፍቀዳቸውን ጥሩ ዜና በመስማታቸው የኤፍ.ኤች.ኤፍ ሠራተኞች ተደስተዋል።

ከአጋሮች ጋር የጥቃት ጥበቃ አቅም ግምገማ ማድረግ

የድርጅቶችን የጥቃት ጥበቃ አቅም የመገምገም ሂደት ለመጨረስ፣ የአጋሮችን ልምድ እና ሙያ ባከበረ መልኩ ግምገማ የማድረግና ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነትዎን በአግባቡ መረዳቱ አስፈላጊ ነው።

አዲሱ የጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራም ትኩረት በተደረገባቸው አካባቢዎች በሚሠሩ አራት የኤፍ.ኤች.ኤፍ አጋሮች በኩል ለገጠሩ ማኅበረሰብ ይሰጣል።

የፕሮግራም አጋሮቹ ልምድ ያላቸው የጤና አገልግሎት ሰጭዎች ናቸው። እንዲሁም ከጥቃት ጥበቃን በተመለከተ የተለያየ ሙያ እና ልምድ አላቸው። ኤፍ.ኤች.ኤፍ የራሱ አጋር ድርጅቶች የጥቃት ጥበቃ ሙያ የላቸውም ብሎ መገመት የለበትም።

ጠቃሚ ምክር፦

ውጤታማ እና ተዛማጅነት ላለው ከጥቃት ጥበቃ የአጋር ድርጅቶች ሙያ በዋጋ ሊተመን የማይችል ነው። አብዛኛውን ጊዜ አጋር ደርጅቶች በከፍተኛ ደረጃ ከተገለሉ ሰዎች ጋር በጣም በቅርበት የተሳሰሩ ናቸው። የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲዎችን እና አሠራሮችን በተለያዩ እና በተዛማጅ ሁኔታዎች ውስጥ ለመተግበር የሚያስችል ክህሎት፣ ዕውቀት እና ሙያ አላቸው።

ለተጨማሪ መረጃ፣ ይመልከቱ በስኬታማ አጋርነት የተመሠረተ የጥቃት ጥበቃን ማጠናከር-የለውጥ መግለጫ።

የጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራም ተቀዳሚ አጋር እንደመሆኑ መጠን ኤፍ.ኤች.ኤፍ ተገቢ የሆኑ የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች በዝቅተኛ ደረጃ ለሚገኙ አጋሮች መድረሳቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። ይህ ማለት ኤፍ.ኤች.ኤፍ በዝቅተኛ ደረጃ በሚገኙ አጋሮች ውስጥ የጥቃት ጥበቃ አቅም ግምገማ ማካሄድ አለበት ማለት ነው። ኤፍ.ኤች.ኤፍ ስምምነት ከመፈረሙ እና የፕሮጀክት ትግበራ ከመጀመሩ በፊት በአጋሮቹ በኩል ሊኖር የሚችለውን ሥጋት እንዲሁም የዓለም አቀፍ የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎችን እየተገበሩ መሆናቸውን መገምገም አለበት። ከጅምሩ ኤፍ.ኤች.ኤፍ ለአጋሮቹ ከእነርሱ ምን እንደሚጠበቅ በግልፅ ማስረዳት አለበት። አጋሮቹ ከእነሱ የሚጠበቁ መስፈርቶችን ማሟላት ካልቻሉ፣ ኤፍ.ኤች.ኤፍ የእነርሱን አቅም ለመገንባት እና የጥቃት ጥበቃ ዝግጅቶቻቸውን ለማጠናከር የሚረዳ ድጋፍ መስጠት አለበት።

ጠቃሚ ምክር፦

ያስታውሱ! ግምታዊ አካሄዶችን ከመከተል መቆጠብ አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ ድርጅት የእርሱ አጋር የሆኑ ድርጅቶች ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሰዎች ከጥቃት ለመጠበቅ ሁሉንም ዓይነት ምክንያታዊ አሠራሮች እየተከተሉ መሆናቸውን የማጣራት ኃላፊነት አለበት። ይህ የሁላችንም የጋራ ኃላፊነት ነው።

የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች፤ ድርጅቶች የፕሮግራሞቻቸውን፣ የእንቅስቃሴዎቻቸውን፣ የሠራተኞቻቸውን እንዲሁም የአጋሮቻቸውን ደህንነት ለማረጋገጥ በቦታው ምን ሊኖራቸው እንደሚገባ ይገልጻል።

የፕሮግራም ምስረታ

ኤፍ.ኤች.ኤፍ ለአዲሱ ፕሮግራም መሪ ድርጅት ነው። ከታች እርከን (በማኅበረሰቡ ውስጥ) ፕሮግራሙን ለሚያስፈጽሙ አጋሮች ግልፅ የሆኑ የጥቃት ጥበቃ መስፈርቶችን ማስቀመጥ አለበት። አጋር ድርጅቶች የጥቃት ጥበቃ መስፈርቶችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ኤፍ.ኤች.ኤፍ በምን መልኩ ድጋፍ ሊያደርግላቸው እንደሚችል ማሳየት አለበት።

የኤፍ.ኤች.ኤፍ ቡድን ጫና ውስጥ በመሆኑ በተለያዩ የቡድኑ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል። በተለያዩ መንገዶች ኃይል/ሥልጣን የሥራ ግንኙነቶች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።

በክፍል 2 ውስጥ፣ የጥቃት ጥበቃ በምን መልኩ ደህንነቱ ከተጠበቀ ፕሮግራም ጋር ሊተሳሰር/ሊስማማ እንደሚችል እና **ስለ ጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራም** (IIP) የተለያዩ የፕሮግራም ዑደት ክፍሎች ይመረምራሉ። የጥቃት ጥበቃ እና ኃይል/ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም በኤፍ.ኤች.ኤፍ የሥራ ቦታ ውስጥ ምን እንደሚመስል ትተዋወቃላችሁ::

ኤፍ.ኤች.ኤፍ የገንዘብ ድጋፍ አግኝቷል በመሆኑም **የጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራም** (IIP) **በማስጀመር ላይ ነው::**

ትኩረት በተደረገባቸው፣ ከፍተኛ ስጋት ባለባቸው የአገሪቱ ወረዳዎች ውስጥ ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ጨቅላ ሕፃናትን ሞት ለመቀነስ የሚረዳውን ይህንን በጣም ጠቃሚ ፕሮግራም ኤፍ.ኤች.ኤፍ በበላይነት ስለሚመራው ዝናሽ በጣም ደስተኛ ናት:: ይህን በመሰለ ለሕፃናት ጠቃሚ በሆነ የክትባት ፕሮግራም ላይ እየሠራ ያለ ድርጅት አካል በመሆኗ ኩራት ይሰማታል::

ዝናሽ፣ በመጀመሪያው የትግበራ/የአፈጻጸም ዓመት አዎንታዊ ውጤቶችን ማየት እንደምትፈልግ እና ኤፍ.ኤች.ኤፍ ምንም ዓይነት ስህተትን እንደማይታገስ ለቡድን አባላቶቿ ግልፅ አድርጋለች::

የፕሮግራሙ አፈሰር የሆነችው አስቴር በአዲሱ ፕሮግራም የንድፍ እና የዕቅድ ዝግጅት ምዕራፍ ላይ እየሠራች ነው፡፡ ደህንነቱ የተረጋገጠ የፕሮግራም ዝግጅት እንዲኖር ከአጋሮች ጋር አብሮ መሥራት አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝባለች፡፡ ለሁሉም ሠራተኞች ተዘጋጅቶ በነበረው የጥቃት ጥበቃ ሥልጠና ላይ ተመልክተው ስለነበሩት የጥቃት ጥበቃ መስፈርቶች ምክር እና ድጋፍ ለማግኘት የጥቃት ጥበቃ ዋና ተጠሪ ከሆነችዉ ከዚነት ጋር ለመገናኘት አስቴር ተዘጋጅታለች፡፡

"የዕቅድ ሂደቱን ለማገዝ በአሁኑ ሰዓት በፕሮግራሙ ዑደት የተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ መወሰድ ያለባቸውን የጥቃት ጥበቃ እርምጃዎች ምልከታ እያደረኩ ነው።"

"ይሄ በጣም ጥሩ ነው ነገር ግን ተልዕኮውን ለማስፈጸም አጋር ተቋማት ወሳኝ ስለሆኑ መካተት እንዳለባቸው አስታውሽ፡፡"

የፕሮግራም ዑደት

ኤፍ.ኤች.ኤፍ ደህንነቱ የተጠበቀ የፕሮግራም ቀረጻ፣ እንደ አዲሱ የጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራም የመሳሰሉ፣ ፕሮግራሞችን ለመተግበር የሚያስችል ምቹ ከባቢያዊ ሁኔታዎችን ለማጠናከርና ለመገንባት እንደሚረዳ ያውቃል። ይህም ማለት ስጋቶችን በጥንቃቄ መለየትና መቆጣጠር ያስፈልጋል ማለት ነው። ኤፍ.ኤች.ኤፍ ሁሉም ፕሮግራሞቹ ለተጠቃሚዎችና ለማኅበረሰቦች ደህንነቱ የተጠበቀ ከባቢያዊ ሁኔታን መፍጠር ወይም አስተዋጽዖ ማድረግ በሚያስችሉ መልኩ ፕሮግራሞቹን ለመንደፍ ይሞክራል።



ያስታውሱ፡-

ሆን ተብሎ ወይም ባለማወቅ የሚወሰዱና ሰዎችን ለጉዳት ሊያጋልጡ የሚችሉ ድርጊቶችን ለመከላከል የሚያስችል ፕሮግራም ለመዘርጋት በእያንዳንዱ የፕሮግራም ዑደት ደረጃ የጥቃት ጥበቃ ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው።

የፕሮግራሙ ዑደት ደረጃዎች፡- መጀመር፣ ማቀድ፣ መተግበር እንዲሁም መቆጣጠር መገምገም እና ማጠናቀቅ/መዝጋት ናቸው።

በፕሮግራም ወይም በፕሮጀክት ትግበራ ምክንያት የሚነሱ ስላልሆኑ ሁሉም ስጋቶች በእኛ ቁጥጥር ሥር አይደሉም። ይሁንም እንጅ፣ በፕሮግራም ቀረጻ እና አተገባበር ሂደት የስጋት መቆጣጠሪያ መንገድ ማካተት አስፈላጊ ነው። በግምገማ ወቅት የስጋት ደረጃው በጣም ከፍተኛ መሆኑ ከታወቀ እና/ወይም ስጋቶችን በተገቢው መንገድ መገምገም ወይም መቀነስ የማይቻል ከሆነ ፕሮግራሙን ላለመተግበር መዘጋጀትም አስፈላጊ ነው።

ደህንነቱ የተጠበቀ የፕሮግራም ቀረጻ

ማስጀመር በዚህ ደረጃ፣ ፕሮግራሙ ይቀረጻል እንዲሁም ግቦች እና የሚያስፈልጉ ግብአቶች ይለያሉ።

ማቀድ በዚህ ደረጃ የሥራ ዕቅዶች እና የበጀት ዝርዝር ይዘጋጃል። የስጋት ግምገማዎች ይካሄዳሉ፣ በተጨማሪም የክትትልና ግምገማ ማዕቀፎችም መዘጋጀት አለባቸው።

ትግበራ እና ቁጥጥር ይህ የሚሆነው የፕሮጀክቱ ትክክለኛ ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ ነው። የፕሮጀቱን ግቦችን ለማሳካት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣ መሣሪያዎች እና ግብአቶች ይቀየራሉ። በዚህ ምዕራፍ፣ የፕሮግራም ዝግጅቱን ለማሻሻል የሚረዳ ቀጣይነት ያለው ክትትል እና ትምህርት ይወሰዳል።

ግምገማ እና ማጠናቀቂያ/መዝጊያ በፕሮግራሙ መጨረሻ ላይ፣ የማጠቃለያ ግምገማ ይካሄዳል እንዲሁም የተገኘው እውቀትና ተሞክሮ ይቀመርና ለሌሎች የማጋራት ሥራ ይሠራል። የማጠቃለያ ሪፖርቶች ተጽፈው ገቢ ይደረጋሉ።



ደህንነታቸው ስለተጠበቀ ፕሮግራሞች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ደህንነታቸው የተጠበቀ ፕሮግራሞችን እንዴት ማሰብ ይቻላል የሚለውን ይመልከቱ።

አሁን አስቴር የፕሮግራሙን ዑደት መሠረት በማድረግ በጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራም ውስጥ የጥቃት ጥበቃን ታሳቢ ማድረግ እንዳለባት ተገንዝባችኋል። ፕሮግራሙን በማስጀመር፣ በማቀድ፣ በመተግበር/በመፈጸም (ክትትልና ግምገማን ጨምሮ) እና በማጠናቀቅ/በመዝጋት ምዕራፎች ውስጥ ስለጥቃት ጥበቃ ማሰብ አለባት።

2.1 የፕሮግራም ዑደት ተግባራት

ጆሴፊን የፕሮግራሙን ዑደት መርሃ-ግብሮች በአራቱ የጨቅላ ህፃናት ክትባት ፕሮግራም ዑደት ደረጃዎች ስር መመደብ እንድትችል የዝርዝር ሊቃፊ ቁልቁል አመልካቹን በመጫን እና መልስ በመምረጥ እገዛ ያድርጉላት።

መልሶቹን ለመመልከት፣ እዚህ ይጫኑ።

ከዚህ ቀጥሎ የሚገኘውን ሰንጠረዥ በማንበብ መልሶችዎን ያረጋግጡ፡-

የፕሮግራም ዑደት ደረጃ	የፕሮግራሙ የዑደት ትግበራዎች	የጥቃት ጥበቃ ትግበራዎች
ማስጀመር	የማኅበረሰብ ምልከታ	ስለአካባቢው መረጃ ያሰባስቡእንዲሁም ማኅበረሰቦችን በማስተባበር በፕሮግራሙ ቦታ(ዎች) ያሉትን ሁኔታዎችን በተሻለ መረዳት።
	የጥቃት ጥበቃ በጀት	ከመጀመሪያው ጀምሮ ለጥቃት ጥበቃ ተግባራት በቂ የገንዘብ እና የሰውኃይል መኖሩን ማረጋገጥ፡፡
ማቀድ	ለተጨማሪ ጉዳት የሚያጋልጡ ስጋቶችን መገምገም	የደህንነት ጥበቃ መንገዶች በቦታው መኖራቸውን በማረጋገጥከፕሮግራሙ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎችእንዲሁም የፕሮግራም ቀረፃው ጉዳት እንዳያስከትል መሥራት
	የድርጊት መርሐ-ግብር	ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ፕሮግራሙን ለመተግበር በሚለኩ ዓላማዎች፣ የጊዜ ሠሌዳዎች፣ የሥራ ድርሻዎች እና ኃላፊነቶች ግልጽ የሆነ የፕሮግራም አቅጣጫ መኖሩን በማረጋገጥ
	ክትትል፣ ግምገማ እና ትምህርት	የክትትል፣ ግምገማ እና ትምህርት ማዕቀፍ መቀረጹን ማረጋገጥ እናማንኛውንም የጥቃት ጥበቃ እርምጃዎችን ታሳቢ ማድረግ ለፕሮግራሙ ጠቃሚ የሆኑ ሥነ-ምግባሮች በቀረጻው ውስጥ መካተታቸውን ያረጋግጣል።

ትግበራ እና ቁጥጥር	የሪፖርት ማድረጊያ መንገድ/ዘዴ	ተጠቃሚዎችን፣ ማኅበረሰቦችን እና ሠራተኞችን ስጋቶቻቸውን እንዲያቀርቡ እና የጉዳት ሪፖርቶችን መደበኛ በሆነ መንገድ እንዲያቀርቡ ያስችላል።
	ሥርፀት እንዲሁምየማነቃቂያ ሥልጠና	ሁሉም ሠራተኞች እና አጋሮች የጥቃት ጥቢቃ ሥልጠና አካል የሆነ የሥርፀት እንዲሁም የወቅታዊ ሥልጠና መውሰዳቸውን ማረጋገጥ በቂ የሆነ እውቀት፣ በራስ
	የቁጥጥር እናትምህርት	የቁጥጥር፣ የግምገማ እና ትምህርት እንዲሁም የምርምር ከንዋኔዎች ለሁሉም ተሳታፊዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ሥነ-ምግባርን የተላበሱ መሆናቸውን እንዲሁም ፣ ተጠቃሚዎች መረጃ በመሰብሰብ ሂደትበዕውቀት ላይ የተመሠረተ ፈቃድ መስጠታቸውን፣ ሁሉም መረጃ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መያዙንና ጥቅም ላይ መዋሉን ያረጋግጡ፡፡
ግምገማ እናመዝጋት/ ማጠናቀቅ	ክለሳ	የፕሮግራሙ ማጠናቀቂያ/መዝጊያ ሲደርስ፣ቁልፍ የሆኑየፕሮግራሙን አፈጻጸሞችን እንዲሁም የተወሰዱ ትምህርቶችን/ተሞክሮዎችን ጨምሮ እያንዳንዱን ነገር መገምገም ያስፈልጋል።፡፡
	የተቀሰሙ ትምህርቶች/ተሞክሮዎች	ለተቋማዊ ትምህርት እና ቀጣይ መሻሻል አስተዋፅዖ ለማድረግ የጥቃት ጥቢቃ ክስተቶችን ግምገማዎችን ፣ ክትትሎ ችን ጨምሮ ከመርሃግብሩ፣ የሚገኙ ትምህርቶችን መያዝ/መሰነድ።

አስቴር የፕሮግራም ዑደት አጀማመር እና ዕቅድ ዝግጅት ምዕራፍ አካል በማድረግ ኤፍ.ኤች.ኤፍ አራቱን አጋር ተቋማት ለፕሮግራሙ ትግበራ ለማዘጋጀት ምን ማድረግ እንዳለበት እያሰበች ነው፡፡ አስቴር አጋር ተቋማቱ በስጋት ግምገማ፣ በማቀድ እና በማስተባበር ዙሪያ ያላቸውን ዕውቀት መጠቀም ትፈልጋለች፡፡ ከመጀመሪያው አንስቶ እነሱን ለማሳተፍ እና እንደ አቻ ተቋማት አድርጋ ለመቁጠር ፍላጎት አላት፡፡

አስቴር የአጋሮች የጥቃት ጥበቃ ማዕቀፎች እንዴት እንደተዘጋጁ እርግጠኛ አይደለችም፡፡ የጥቃት ጥበቃ መከላከያ እና ምላሽ መስጫ ሥርዓቶቻቸውን ለማሻሻል የሚረዳ ድጋፍ ሊያስፈልጋቸው እንደሚችል ታውቃለች፡፡ ይህንንም ከአጋሮች ጋር እንዴት በተሻለ መንገድ መፈጸም እንደምትችል ከዚነት ምክር ለመጠየቅ ወስናለች፡፡

ዚነትም ስለተለያዩ ዓለም አቀፍ የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች ለአስቴር ከነገረቻት በኋላ ኤፍ.ኤች.ኤፍ ተቀብሎ ያጸደቃቸውን የመመዘኛ ሠነዶች ሠጠቻት፡፡ በተጨማሪም ለአገራቸው እና ለፕሮግራማቸው በሚጠቅም መልኩ የተዘጋጀውን ተያያዥነት ያለው የጥቃት ጥበቃ ግለ-መመዘኛ የመጠይቅ ቅጽ ለአስቴር ሰጠቻት፡፡ አጋሮች ይህንን የመጠይቅ ቅጽ ሞልተው ሲጨርሱ፣ አስቴር የጥቃት ጥበቃ ክፍተቶችን መለየት እንደምትችል ዚነት ገልጻላታለች፡፡ ይህም ለኤፍ.ኤች.ኤፍ እና ለአጋሮች የጥቃት ጥበቃ ዕቅድ ለማዘጋጀት ሊረዳት ይችላል፡፡ አስቴር የጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራም (IIP) አጋር ተቋማት ስላላቸው አቅም ባላት መረጃ መሠረት እነዚህን ግዴታዎች ለመወጣት ሊሠራ ስለሚገባው የሥራ መጠን ተጨንቃለች፡፡

"የጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራም (IIP) አጋር ተቋማት የጥቃት ጥበቃ ግለ-መመዘኛ ቅጽ እንዲሞሉ ስጠይቃቸው ምን ሊመልሱ እንደሚችሉ ያሳስበኛል፡፡ እነሱ ደስተኞች ይሆናሉ ብዬ አላምንም፡፡"

የጥቃት ጥበቃ ግለ-መመዘኛ ቅጽ እንዲሞሉ ሲጠየቁ የኢጋር ተቋማት ስሜት የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል …

የመረጃ እና ድጋፍ ማዕከል የጥቃት ጥበቃ እንቅስቃሴ ደረጃ መመዘኛዎች።

የጥቃት ጥበቃ ግለ-መመዘኛ

አስቴር ለእያንዳንዱ አጋር ተቋም የጥቃት ጥበቃ ግለ-ምዘና ቅጽ ልትሰጣቸው ትችላለች። አንድ ተቋም የዓለም አቀፍ የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎችን ለማሟላት ምን ያህል የቀረበ እንደሆነ ለማየት እና የት ቦታ መሻሻል እንደሚያስፈልገው ለመለካት ይህ ጥሩ መንገድ ነው። አጋር ተቋማት የግለ-ምዘና ቅጹን ሞልተው ሲጨረሱ፣ የጥቃት ጥበቃ እንቅስቃሴያቸውን እንዲያጠናክሩ ለመደገፍ ኤፍ.ኤች.ኤፍ ምን መሥራት እንዳለበት ለመፈተሽ አስቴርን ይረዳታል።

ይህን ይጫኑ የተቋማዊ ጥምረት ቋሚ ኮሚቴ (IASC) የዝቅተኛ ደረጃ ትግበራ መመዘኛዎች፡- የወሲባዊ ብዝበዛ እና ትንኮሳን (SEA) ለመከላከል በአውን ፕርሶኔል የወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃትን ለመከላከል የሚረዱ መመዘኛዎችንና ጠቋሚዎችን ያካተተ ሠነድ ። ይህንን የመመሪያ ሠነድ ለማንበብ ጥቂት ደቂቃዎችን ይውሰዱ።

2.2 የግለ-ምዘና ተግባራት

ራስዎን የኤፍ.ኤች.ኤፍ አንዱ አጋር ተቋም እንደሆኑ እና አስቴር የጥቃት ጥበቃ ግለ-ምዘና ቅጽ እንዲሞሉ እንደሰጠችዎት አድርገው ያስቡ፡፡

በዚህ ሞጁል ክፍል ፣ ውስጥ ስለ መረጃና ድጋፍ ማዕከሉ የጥቃት ጥበቃ እንቅስቃሴዎች እንዲተዋወቁ ተደርጓል፡፡ ይህ የተቋም አቅም ግምገማ ይህንን መንገድ እንደሚከተል ያያሉ፡፡

እዚህ ይጫኑ የእርስዎ ተቋም እነዚህን የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች ለማሟላት ምን ያህል የቀረበ እንደሆነ ለማየት፡፡

መሻሻሎችን ለመከታተልና ለመለካት እንዲሁም የጥቃት ጥበቃ የድርጊት መርሐ-ግብርን ለማሻሻል በየጊዜው ግለ-ምዘና ማካሄድ ጠቃሚ ነው፡፡

ሃሳብዎን ያንፀባርቁ፡- በተቋምዎ ውስጥ የጥቃት ጥበቃ መሻሻሎችን ለመከታተልና ለመለካት ግለ-ምዘናን በምን መልኩ ሊጠቀሙበት ይችላሉ?

አስቴር ከቅርብ ኃላፊዋ ጋር በነበራት ስብሰባ ተቋማት የጥቃት ጥበቃ ግለ-ምዘናን እንዲያጠናቅቁ መጠየቅ ስለሚኖረው ጠቀሜታ ሃሳቧን ገልጻለች፡፡ የፕሮግራሙ ማናጀር የሆነው አህመድ ግን ሃሳቧን አጣጥሎታል፡፡ አጋር ተቋማትን የጥቃት ጥበቃ ግለ-ምዘና እንዲያጠናቅቁ መጠየቅ ከልክ ያለፈ ቢሮክራሲያዊ አካሄድ ነው ብሎ ያምናል።

"የጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራም (ዘIP) አጋር ተቋማት ግለ-ምዘና ማጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ አለብን ::"

"አይሆንም፣ ይሄ ጊዜ ማባከን ነው የሚሆነው። አሁን ተገቢውን የተቋማዊ አቅም ምዘና አልፈናል፣ እናም ጉዳዩን በዚህ እንተወው እያልኩ ነው::"

"ከአጋር ተቋማት የሚጠበቁ መስፈርቶች በኤፍ.ኤች.ኤፍ የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች ውስጥ ቢካተቱ ኖሮ የአጋር ተቋማት ግምገማ አስፈላጊ መሆኑን አህመድ ይገነዘብ ነበር::"

"እነዚህ ሁሉ ተጨማሪ ፍላጎቶች ከልክ ያለፉ እና አላስፈላጊ ናቸው እንዲሁም የጀማሪ ሠራተኛ መለያ ባህርያት ናቸው:: ከአጋር ተቋማት የሚጠበቁ መስፈርቶች በኤፍ.ኤች.ኤፍ የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች ውስጥ እንኳ አልተካተቱም::"



አህመድ በፕሮግራም አስተዳደር ውስጥ ጠንካራ ልምድ ያለው ሲሆን ባለፉት ዓመታት ውስጥ ከአራቱ አጋር ተቋማት ጋር በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ገንብቷል፡፡ ከአንዳንድ ሠራተኞች ጋር እንኳ ጥሩ ጓደኝነትን መሥርቷል፡፡

ጠቃሚ ምክር፡-

በታማኝነት ወይም በጓደኝነት ላይ የተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶች ወሳኝ በሆነ የሥራ ሂደት ላይ እውነት ወዳልሆኑ ግምቶች ሊያመራን ይችላል፡፡ በሥራ ቦታ ውስጥ ያሉ የማህበራዊ ግንኙነቶች ባለማወቅ የእርስ በእርስ የመጠቃቀም ወይም በሥራ ሂደት ውስጥ ሊኖር የሚችልን ጉድለት ችላ የማለት ባህል እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሠራተኞች በሥራ ቦታ ውስጥ ሊፈጠሩ ለሚችሉ እንደዚህ ዓይነት ተጽዕኖ ፈጣሪ ሁኔታዎች ንቁ መሆን አለባቸው፡፡

በአህመድ አረዳዶችና እና ምላሾች አስቴር ስጋት ገብቷታል፡፡ የፕሮግራም ኃላፊነቷን ለመወጣት በምን መልኩ መቀጠል እንዳለባት እንዲሁም ስለሥራ ድርሻዋ እና ስለተቋሙ ባላት ስሜት ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተጽዕኖ ስለሚኖረው ይህ ጉዳይ እሷን አስጨንቋታል፡፡

ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም በጣም ስውር በሆነ መንገድ ሊፈጸም ይችላል። ስለዚህ የጥቃት ጥበቃ ስጋት ሲኖር ሪፖርት ለማድረግ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ እንዲሁም በተቋማት መካከል በሚኖሩ የሥራ ግንኙነቶች ውስጥ ሥልጣንን በተለያዩ ብዙ መንገዶች ጥቅም ላይ ማዋል ይችላል፡፡

2.3 የሥልጣን ተግባር

አህመድ በፕሮጀክቱ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ፍላጎት የለውም ምክንያቱም ይህ በጣም ጀማሪ የሆነ ሠራተኛ ኃላፊነት አድርጎ ስለሚመለከት ነው፡፡

ከዚህ በታች የቀረቡት አህመድ ከአስቴር ጋር ሲነጋገር ሊያነሳቸው የሚችሉ የንግግር ይዘቶች ናቸው፡፡ እሱ ሥልጣኑን በምን መልኩ እየተጠቀመ እንደሆነ እና ይህም አስቴርን ምን ዓይነት ስሜት እንዲሰማት እንደሚያደርግ ያስቡ፡፡

የዚህ ዓይነት የንግግር ይዘቶች እርስዎን ቢያጋጥምዎት፣ ምን ሊሰማዎት ይችላል?

መልሶቹን ለመመልከት፣ **እዚህ ይጫኑ።**

ከሥልጣን ጋር በተያያዘ ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ሌላው ነጥብ በተቋማዊ ተዋረድ/ሰንሰለት ውስጥ የተዘረጋ መሆኑን ነው። ሥልጣንን ለመሻሻል፣ ለማበረታታት እና ለለውጥ በአዎንታዊ መልኩ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል። ይሁንም እንጅ ሥልጣን በተለያዩ አግባብነት በሌላቸው መንገዶችም ሊተገበር ይችላል። ሥልጣንን ያለአግባብ ከመጠቀም ጋር የተገናኙ ሌሎች ምሳሌዎች፡- እንደ ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችል የሆነ ጉዳይ ያላቸውን የሥራ ባልደረቦችን አፍ ማዘጋት/ዝም ማሰኘት፤ የሥራ ባልደረቦችን እና/ወይም ተጠቃሚዎችን መተንኮስ እና ማጥቃት፤ እና/ወይም ሥልጣንን በመጠቀም በተቋሙ ውስጥ ወይም በሰፊው ማኅበረሰብ ውስጥ አንድን ሰው ለጥቃት ማዘጋጀት የመሣሉትን ሊጨምር ይችላል።

አህመድ ለአስቴር የሰጣትን ምላሽ እንደገና እንመልከት፡፡ እሷ ኡጋር ተቋማት ግለ-ምዘናውን እንዲያጠናቅቁ ትፈልጋለች። አህመድ ደግሞ ሥራ አስኪያጅ/ማኔጀር እንደመሆኑ መጠን ነገሮችን በፍጥነት ማስኬድ እንዳለበት ይሰማዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ሥልጣን በኤፍ.ኤች.ኤፍ የድርጅት መዋቅር ውስጥ የተገነባ መሆኑን ነው፡፡ ስለተቋማዊ የአሠራር ባህል በሚቀጥለው የሞጁሉ ክፍል በበለጠ የምንመለከት ይሆናል፡፡



"ጊዜ ወሳኝ ነገር ነው ስለሆነም ልናሳካቸው የሚገቡ ዓላማዎች አሉ፡፡"

"ያንን ተረድቻለሁ፣ ነገር ግን አንዳንድ ነገሮችን በመዝለል ሥራን በጣም በፍጥነት ለማጠናቀቅ መሞከር ስጋቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡"

ጠቃሚ ምክር፡-

በፍጥነት ለማደግ ወይም ድርጊቶች ለማከናወን በከፍተኛ ጫና ውስጥ በሚገኙና ሥራ በሚበዛባቸው ተቋማት ውስጥ እንደ የጥቃት ጥበቃ የመሣሠሉ የደህንነት እርምጃዎች፤ በተለይ ከቁጥጥር፣ ከግምገማ እና ከክለሳ ጋር በተያያዘ የሚኖራቸው ጠቀሜታ ሊቀንስ ይችላል፡፡ ከተቋማት አስተዳዳሪዎች ጋር ስለእነዚህ የጥቃት ጥበቃ እርምጃዎች አስፈላጊነት ሲነጋገሩ፣ እነዚህ መቆጣጠሪያዎች በቦታው ከሌሉ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ለይቶ ማሳወቅ ጠቃሚ ነው፡፡

የተቋማዊ የአሠራር ባህል

ዝናሽ የኤፍ.ኤች.ኤፍ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እንደመሆኗ መጠን ለጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራም (IIP) እና ለጥቃት ጥበቃ ጉዳዮች አጠቃላይ ኃላፊነት አለባት፡፡ ቡድኑ ሥራውን በአግባቡ እንደሚወጣ በመተማመን፣ ሥራው በጥሩ ሁኔታ ስለመጀመሩ ግን ማረጋገጫ ትፈልጋለች፡፡

በዚህ ሞጁል የመጨረሻ ክፍል ውስጥ፣ ስለኤፍ.ኤች.ኤፍ የተቋም ባህል እና አመራር አስፈላጊነት ይመለከታሉ፡፡ እንዲሁም የጥቃት ጥበቃ መስፈርቶች በተጠያቂነት፣ በክትትል፣ እና በሙያዊ አሠራር/ትግበራ ላይ እንዴት ተጽዕኖ ማሳደር እንደሚችሉ ይፈትሻሉ፡፡ በተጨማሪም የተቋም መሪዎች ለጥቃት ጥበቃ ኃላፊነት ሲወስዱ የሚኖረውን ጠቀሜታ ይመለከታሉ።

የኤፍ.ኤች.ኤፍ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሆነችው ዝናሽ በጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራሙ ላይ ከፍተኛ ፍላጎት ያሳየች በመሆኗ በሂደቱ ላይ ወቅታዊ መረጃ እንዲደርሳት ጠይቃለች፡፡ የጊዜ እና የተፈላጊ አቅርቦቶች እጥረት እንደሚኖር ታውቃለች ነገር ግን የለጋሽ ድርጅቶችን ታሳቢ አድረጋለች፡፡ በተጨማሪም ዝናሽ የፕሮግራም ቡድኑ ደጋፊ መሆን ትፈልጋለች፡፡

ዝናሽ በጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራሙ ላይ የነቃ/የላቀ ፍላጎት እያሳየች መሆኑ በጣም ጥሩ ነው። የሰዎችን ደህንነት መጠበቅ እና የጥቃት ጥበቃ ኃላፊነቶች እንዲኖሩ ማድረግ ደህንነቱ የተጠበቀ ተቋም ለመምራት የሚያስችሉ መሠረታዊ ክፍሎች መሆናቸውን ታውቃለች። ነገሮች ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ከሄዱ ተጠያቂ ትሆናለች ስለዚህ ነገሮችን ለማስተካከል የሚረዳ ኃላፊነት መውሰድ ይጠበቅባታል።

ዝናሽ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራሙ ጋር ሊያያዙ የሚችሉ የጥቃት ጥበቃ ስጋቶችን እየፈተሸች ነው። የቡድኑ አባላት ፕሮግራሙን በሚያስኬዱበት ወቅት የተጠቃሚዎችን፣ የሠራተኞችንና የማኅበረሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ሁሉንም ዓይነት ምክንያታዊ እርምጃዎች እየወሰዱ መሆኑን ለማወቅ ከፕሮግራም ቡድኑ ማረጋገጫ ትፈልጋለች።

"የጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራሙ በጥሩ ሁኔታ እየተጓዘ መሆኑን የግድ ማረጋገጥ አለብኝ ምክንያቱም ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር ከመነጋገሬ በፊት በሂደቱ ላይ ዕውነተኛ የሆነ የራስ መተማመን ሊኖረኝ ይገባል። አህመድን በሚቀጥለው የከፍተኛ አመራር ቡድን ስብሰባ ላይ እጠይቀዋለሁ።"

3.1 የጥቃት ጥበቃ ዝርዝር ተግባራት ማረጋገጫ

ግሬስ በዚህ ደረጃ የምትፈልጋቸውን አምስት የማረጋገጫ መንገዶች ከታች ከተዘረዘሩት ውስጥ ይምረጡ።

የመርሃ ግብር ሪፖርት ማድረጊያ/ጥቆማ ማቅረቢያ መንገዶች ተዘርግተዋል	☐	ሁሉም አጋር ድርጅቶች የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲዎች እና የአሰራር ሥርዓቶች አሏቸው	☐
የአጋር ድርጅት የድርጅታዊ አቋም ዝርዝር ጥናት ተጠናቋል	☐	ከመርሃ ግብር ጋር ሊያያዝ የሚችል የስጋት ግምገማ ተጀምሯል	☐
ሁሉም አጋር ድርጅቶች የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲዎች እና የአሰራር ሥርዓቶች አሏቸው	☐	የቤተሰብ ጤና ፍሮንተር(FHF) የጥቃት ጥበቃ መሪ አለው/ ተሰይሟል/ተቋቁሟል	☐
ከሁሉም አጋሮች ጋር የተደረጉ ስምምነቶች የጥቃት ጥበቃን የተመለከቱ አንቀጾችን/ድንጋጌዎችን ያካተቱ ናቸው	☐	አጋር ቡድኖች በጥቃት ጥበቃ ዙሪያ ስልጠና አግኝተዋል	☐

መልሶቹን ለመመልከት፣ **እዚህ ይጫኑ።**

ዝናሽ በሚቀጥለው የከፍተኛ አመራር ቡድን ስብሰባ ላይ ስለጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራሙ ወቅታዊ መረጃ እንዲሰጣት አህመድን ጠየቀችው፡፡ ዝናሽ በሳምንቱ መጨረሻ መደበኛ የሆነ የፕሮጀክት ማብራሪያ እንድትጠይቅ ያነሳሳት ጉዳይ ምን እንደሆነ አህመድ እርግጠኛ የሆነ አይመስልም፡፡



አህመድ ግራ የመጋባት ስሜት ተሰማው፡፡ ስለፕሮጀክቱ በበቂ ሁኔታ ዕውቀት ስለሌለው ሃሰተኛ ማረጋገጫ ሰጠ፡፡ ጊዜ ማግኘት እንዲችል መደበኛ ማብራሪያው ከሚቀጥለው የሩብ ዓመት የፕሮጀክት ክትትል ሪፖርት ጋር በተያያዘ ቢሆን የተሻለ እንደሚሆን ጥቆማ ሰጠ፡፡

አህመድ ሲያመነታ እና እርግጠኛ እንዳልሆነ ስታይ ዝናሽ እምነት አጣች፡፡ ይሁንም እንጅ ጊዜው ገና መሆኑን እንዲሁም ለተቋሙ አዲስ መሆኗን በመገንዘብ መደበኛ ማብራሪያው እሱ በጠቆመው ጊዜ እንዲሆን ተስማማች፡፡



"እሺ ተረድቻለሁ ነገር ግን ከዚህ ፕሮጀክት ትልቅ ነገሮችን እጠብቃለሁ። እንዲሁም ከአንዳንድ አስፈላጊ ሰዎች ጋር በመሆን የከፍተኛ ደረጃ ጉብኝት ይካሄዳል፡፡ ይህ በጣም ጠቃሚ ፕሮጀክት ስለሆነ ምንም ዓይነት ስህተት እንደማይኖር ማረጋገጥ አለብኝ፡፡"

"ዝናሽ አትጨነቂ፣ እኔ አንችን ማሳዘን አልፈልግም።።"



"አ የኔ ውድ፣ ለሥራው ትክክለኛ ሰው አህመድ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ ምክንያቱም ከዚህ ፕሮግራም የሚጠበቀው ብዙ ነገር ስለሆነ እና እኔም የመጨረሻ ደረጃ የተጠያቂነት ኃላፊነት ስላለብኝ።።"

"ለዚህ ጉብኝት የሚረዳ ዕቅድ ማዘጋጀት እንድትጀምር አስቴር ን ባስቸኳይ ማነጋገር የግድ ይኖርብኛል።።"



ሃሳብዎን ያንፀባርቁ፡- ዝናሽ ለአህመድ የሰጠችው ምላሽ ምን ያህል ተገቢ ነበር? የእርሷ ምላሽ በአህመድ ላይ ያላትን እምነት በማሳየት በዛውም ሥራው እንዲከናወን ማረጋገጫ ማግኘት መቻሏን እንዴት ሊያሳይ ይችላል?



"አመሰግናለሁ አህመድ፣ ሁለታችንም ይህ የከፍተኛ ደረጃ ጉብኝት የተሳካ እንዲሆን እንደምንፈልግ አውቃለሁ። የሚያሳስብ ጉዳይ ካለ አሳውቀኝ እና መፍትሄ ለመፈለግ በጋራ መሥራት እንችላለን፡፡"

የከፍተኛ አመራር ቡድኑን ስብሰባ ተከትሎ፣ አህመድ በጨቅላ ሕፃናት የክትባት ፕሮግራሙ ዙሪያ ከአስቴር ጋር ለመወያየት የስብሰባ ጥሪ አቀረበ፡፡ ፕሮጀክቱን አስመልክታ ዝናሽ የከፍተኛ ደረጃ ጉብኝት ለማካሄድ እያሰበች ስለመሆኑ ዜናውን አጋራት፡፡ የፕሮጀክቱን የስጋት መቆጣጠሪያ ቅጽ ለማጋራት እና በውስጡ በአግባቡ ያልተካተቱ አንዳንድ የጥቃት ጥበቃ ስጋቶች እንዳሉ ለማሳሰብ ይህ ጥሩ አጋጣሚ ነው ብላ አስቴር ተቀብላዋለች፡፡

"መልካም ዜና! በጣም አስፈላጊ የሆኑ አንዳንድ ሰዎች የጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራሙን ለመጎብኘት ፍላጎት አላቸው፡፡ ምን መሥራት እንደምንችል ያለንን አቅም ለማሳየት ይህ ለእኛ ትልቅ አጋጣሚ ነው፡፡"

"አዎ፣ ያ በጣም ጥሩ ነገር ነው፣ ነገር ግን በነገርኩህ የጥቃት ጥበቃ ስጋት ቀጠናዎች ላይ ልንሠራቸው የሚገቡ ብዙ ሥራዎች አሉብን፡፡"

"ሥጋቶች !!"

አስቴር መጨነቋ እንዲሁም ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ወደአህመድ የትኩረት አቅጣጫ ማምጣቷ ትክክል ነው። ስጋቶችንና ተግዳሮቶችን ቀድሞ መለየት አብዛኛውን ጊዜ ሊዘነጋ እንደሚችል ከበፊት ልምዷ ታውቃለች።

አስቴር ስጋቶችን ቀድማ መለየቷ ኤፍ.ኤች.ኤፍ ስጋቶችን እንዲገነዘብ፣ ዕውቅና እንዲሰጥና የሚቻል ከሆነ ስጋቶችን ለመቀነስ ፍላጎት እንዲያድርበት ለማድረግ ስለሚረዳ በጣም ጥሩ ነው። እነዚህን ስጋቶች በፕሮጀክቱ የስጋት መቆጣጠሪያ ቅጽ ውስጥ በመመዝገብ ላይ ነች። ማንኛውም ስጋት የመከሰት ዕድሉን እና የሚያስከትለውን የተጽእኖ ደረጃ መሠረት በማድረግ መገምገም እንዳለበት ታውቃለች።

በኤፍ.ኤች.ኤፍ ውስጥ የጥቃት ጥበቃ የእያንዳንዱ ሰው ኃላፊነት ቢሆንም አስቴር ግን ሁሉንም የሥራ ጫና በመሸከም ዋጋ እየከፈለች ይመስላል። ምንም እንኳ አስቴር ሕጋዊ የውክልና ኃላፊነት ቢኖርባትም፣ ሁሉንም የጥቃት ጥበቃ ኃላፊነቶች አንድ ሰው ላይ ብቻ መጫን ደካማ የሆነ ተቋማዊ አሠራር ነው። የኤፍ.ኤች.ኤፍ አመራሮች የጥቃት ጥበቃ ኃላፊነትን ለሌሎች ማጋራት እንዲሁም ስለስጋቶች እና ተፅዕኖዎቻቸው ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል። ከፍተኛ የሥራ አመራር ቡድኑ ስጋቶችን ወይም ችግሮችን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል፣ በማን እና መቼ የመሣሠሉ ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ ግልጽ የሆነ የድርጊት መርሐ-ግብር ለማዘጋጀት ከአስቴር ጋር አብሮ መሥራት ይኖርበታል። ይህም ኃላፊነትን ለማጋራት እና ተጠያቂነት ያለው አሠራር እንዲኖር ይረዳል።

ዚነት የኤፍ.ኤች.ኤፍ የጥቃት ጥበቃ ዋና ባለሞያ/ተጠሪ ናት። ከዚህ በተጨማሪ፣ ኤፍ.ኤች.ኤፍ የከፍተኛ የሥራ አመራር ቡድኑ አባል የሆነ የጥቃት ጥበቃ ተወካይ መሪ መሾም አለበት። ይህ የሥራ ኃላፊነት ቦታ የጥቃት ጥበቃ በኤፍ.ኤች.ኤፍ ከፍተኛ የሥራ አመራር ቡድን ስብሰባዎች ውስጥ መደበኛ የሆነ አንድ የውይይት አጀንዳ መሆኑን ያረጋግጣል። በጥቃት ጥበቃ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ውይይቶችን በማካሄድ፣ ቡድኑ ለጥቃት ጥበቃ ያለውን ቁርጠኝነት ሊያሳይ ይችላል። እንዲሁም አጠቃላይ በተቋሙ ውስጥ ግልጽ የሆኑ አቅጣጫዎችን/መመሪያዎችን ሊያቀርብ ይችላል። በተጨማሪም በጥቃት ጥበቃ አተገባበር ሂደት እንደ አህመድ ያሉ አመራሮችን ተጠያቂ ለማድረግ ያስችላል።

ጠቃሚ ምክር፡-

የጥቃት ጥበቃን እንዲሁም የሥነ-ምግባራዊና አቃፊ ባህልን አስፈላጊነት በማረጋጥ ረገድ የከፍተኛ አመራር ሚና በጣም ወሳኝ ነው፡፡ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ እንዲሁም ሌሎች ማንኛውም ጥቃት አድራሽ ባህርያትን በጭራሽ ያለመፍቀድ ፖሊሲ አጠቃላይ መመዘኛዎችን በመንደፍ እና ጠቀሜታቸውን አጉልቶ በማሳየት ሂደት እንዲሁም ተቋማዊ ዕሴቶችን ከላይ ወደታች ለማስረጽ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ፣ የከፍተኛ የሥራ አመራር ቡድኑ የጥቃት ጥበቃ መሪ፣ የጥቃት ጥበቃ ዋና ባለሞያ/ተጠሪ መሆን ይችላል፡፡ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲዎችን ለማስፈጸም እንዲሁም የጥቃት ጥበቃ ጉዳዮችን በተመለከተ ለሠራተኞች ምክር እና መመሪያ ለመስጠት ይህ ሰው/ ይህቺ ሰው ኃላፊነት አለበት/አለባት፡፡

3.3 የሥጋት ቁጥጥር፡-

አስቴርን የሚያሳስባት ከፕሮግራሙ ጋር የተገናኙ ብዙ ዓይነት ሥጋቶች አሉ፡፡



በፕሮግራሙ ዙሪያ ያሉ ስጋቶችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አስቴር ግምት ውስጥ ልታስገባቸው ከሚችሉ የስጋት ቅነሳ ምክረ-ሃሳቦች ጋር የሚዛመደውን ትክክለኛ የስጋት ዓይነት ይምረጡ፡፡

ችግሮችን ለመፍታት ከአጋሮች ጋር በጋራ መሥራት	የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃትና ፆታዊ ትንኮሳ አዘል ጥቃቶችን እንዲሁም ሌሎች የጉዳት ዓይነቶችን ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችሉ የተዘረጉና ተደራሽ የሆኑ የሪፖርት ማድረጊያ መንገዶች በቦታዉ አሉ።
ችግሮችን ለመፍታት ከአጋሮች ጋር በጋራ መሥራት	የአገልግሎት አቅርቦት ምልከታ እና የሥነ-ልቦናዊና ማኅበራዊ ድጋፍ ዝግጅቶች በቦታው አሉ።
ችግሮችን ለመፍታት ከአጋሮች ጋር በጋራ መሥራት	የሕጻናትን ክብር የሚነኩና ተገቢነት የሌላቸው ምስሎችን ከበይነ-መረብ ላይ ለማውረድ ግልጽ የሆነ ሪፖርት ማድረጊያ መመሪያ አለ።
ችግሮችን ለመፍታት ከአጋሮች ጋር በጋራ መሥራት	በፕሮግራም ዕቅድ እና ቀረጻ የመጀመርያ ምዕራፍ የተጠቃሚዎችና የማኅበረሰቡ ተሳትፎ ነበረ።
ችግሮችን ለመፍታት ከአጋሮች ጋር በጋራ መሥራት	አግባብነት የሌላቸው ግለሰቦች ለጥቃት ተጋላጭ ከሆኑ ቡድኖች ጋር እንዳይሠሩ ለመለየትና ነጥሎ ለማስቀረት ጤናማ የሆነ የቅጥር ምልመላ እና የማጣራት ዝግጅቶች ተደርገዋል።
ችግሮችን ለመፍታት ከአጋሮች ጋር በጋራ መሥራት	የጥቃት ጥበቃ ዝግጅታቸው ማረጋገጫ እንዲያገኝ ዋና አጋር ተቋማት ከሌሎች አጋሮች ጋር በመሆን ፕሮግራሙን ለመምራት የሚያስችል አቋም መኖራቸውን ፈትሸዋል።

መልሶቹን ለመመልከት፣ እዚህ ይጫኑ፡፡

አህመድ የጥቃት ጥበቃ ሥጋቶችን በመቆጣጠር እና ለዝናሽ የአፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ላይ ማተኮር አለበት። ይሁን እንጅ፤ እሱ በይበልጥ ያተኮረው ዶክተሮችን ከመቅጠር እና ለማቆየት ከሚደረግ የሥራ ሂደት ጋር በተያያዙ ስጋቶች ላይ ነው። ከዚህ በፊት በእነዚህ አካባቢዎች ከቅጥር ጋር የተያያዙ ብዙ ተግዳሮቶች ነበሩ። ይህ ትኩረት የሚፈልግ የስጋት ቀጠና እንደሆነ አስቴር ትስማማለች፤ ነገር ግን የአህመድን ትኩረት፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የዶክተሮች የቅጥር ሂደትን ጨምሮ፣ ወደሌሎች ሰፊ ወደሆኑ የፕሮጀክቱ የጥቃት ጥበቃ ስጋቶች ዙሪያ ለመሳብ እየሞከረች ነው። ይህ ለአስቴር አስቸጋሪ ሆኖባታል ምክንያቱም አህመድ አሁን ከመጭው የፕሮጀክት ጉብኝት ጋር ወደተያያዙ እና በይበልጥ አቅርቦት ላይ ወደሚያተኩሩ ጉዳዮች ተሸጋግሯል።

"ምንጊዜም ቢሆን አስቴር ረዘም ያለ የሥራ ዝርዝር አላት እሱም ሁልጊዜ የሚያተኩረው ስለጥቃት ጥበቃ ነው። በመስክ ላይ በቂ ዶክተሮችን ለማግኘት ምን ያህል እንደምጨነቅ እሷ በግልጽ አልተገነዘበችም። እናምጉብኝቱን አስመልክቶ መሠራት ስላለበት ሥራ እና ዝናሽ እንደምትፈልገው ነገሮችን ለማከናውን ሳስብ... በጣም እጨነቃለሁ።"

ጠቃሚ ምክር፦

ለአንዳንድ ሥራዎች እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች የሚደረግ ቅጥር እጅግ በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል። ግጭቶችንና አደጋዎችን ጨምሮ በብዙ አሳማኝ ምክንያቶች አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ በተለይ በላቀ ሁኔታ ደህንነታቸው የተጠበቀ የቅጥር እርምጃዎች እንዲኖሩ ማድረግ ያስፈልጋል። ምክንያቱም በእንደነዚህ ዓይነት ቀውሶች ውስጥ ጉዳት ለማድረስ ፍላጎት ባላቸው ሰዎች ተቋማት ትኩረት ሊደረግባቸው ስለሚችል ነው።

አህመድ ስለፕሮጀክቱ በጣም እንደተጨነቀ ለአስቴር ግልጽ ሆኖላታል። በመሆኑም ከአንዳንድ አጋር ተቋማትና እና የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ጋር ለመገናኘት የመስክ ጉዞ እንዲያደርጉ ሃሳብ አቀረበች። ይህም በመስክ ላይ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን ለመከታተል ተጨማሪ ዕድል ይፈጥርላቸዋል። አህመድ በሃሳቧ ተስማምቷል በተጨማሪም ከአጋር ተቋማት የሥራ ባልደረቦች ጋር ዳግም የመገናኘት ተስፋ ስለፈጠረለት ተደስቷል።

"የመስክ ጉብኝት ስለማድረግ እና በጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራሙ ዙሪያ ስላሉ ነገሮች ስለማጣራት ምን ታስባለህ? ምን መሠራት እንዳለበት የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት ይረዳል፡፡"

"ጥሩ ሃሳብ ነው። እዚያ ነገሮች ሁሉ በጣም በዝግታ ሊከናወኑ ይችላሉ፣ እናም በጉብኝቱ ወቅት ምንም ዓይነት ችግር እንዲገጥመን አንፈልግም፡፡"

"የተወሰኑ ጓደኞቼን ማግኘት ስለምችል በጣም ጥሩ ነው – ይህንን የስምምነት ውል ካገኙ በኋላ እኔን በድጋሜ በማየታቸዉ ደስተኛ ሊሆኑ ይችላል፡፡"

አስቴር ለመስክ ጉዞው ዝግጅት ጀምራለች በተጨማሪም በፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ (M&E) መስፈርቶች ላይ ምክር ለማግኘት ከደስታ እና ከአሰፋ ጋር ለመነጋገር ወስናለች፡፡

አስቴር የኤፍ.ኤች.ኤፍን የመስክ ጉብኝት ለማዘጋጀት የደስታ እና የአሰፋን ምክር ተከትላለች፡፡ የጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራሙን የቁጥጥር ሂደት ለመደገፍ የሚረዳ የቁጥጥርና የግምገማ (M&E) መስፈርቶችን አዘጋጅታለች፡፡ በተጨማሪም ስለጨቅላ ሕፃናት ክትባት ፕሮግራሙ፣ የአጋር ተቋማትን አቅም እና ቁልፍ የሆኑ የፕሮግራም ጭብጦችን እንዲሁም ስጋቶችን የሚያካትት የማጠቃለያ መረጃ በመዘርዝር ለአህመድ የሚረዳ አጭር ማብራሪያ አዘጋጅታለች፡፡ ከመስክ ጉብኝቱ በፊት አህመድ በማንኛውም ነገር ላይ በቂ መረጃ እንዲኖረው ለማረጋገጥ በዚህ አጭር ጽሁፍ ውስጥ የጥቃት ጥበቃ ጉዳዮችንም በጥንቃቄ ማካተት ችላለች፡፡

ጠቃሚ ምክር፡-

ሠራተኞች ወደ መስክ ጉዞ ከመውጣታቸው በፊት የሥነ-ምግባር ደንቦችን ጨምሮ ስለተቋማቸው የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲዎችና አሠራሮች ራሳቸውን ደግመው ማስተዋወቅ እንዲሁም አስገዳጅ ሥልጠና ወቅታዊ መሆኑን ማረጋገጥ ጥሩ አሠራር ነው፡፡ በተጨማሪም፣ የመስክ ላይ ሪፖርት ማቅረቢያ መንገዶችን ለራስ ማስተዋወቅ/ማላመድ እና ይህን መረጃ የመስክ ጉዞውን ለሚቀላቀሉ ለሌሎች ሰsዎች ማጋራት ይመከራል፡፡

ደህንነቱ ለተጠበቀ የመስክ ቁጥጥር የሚረዱ ጠቃሚ ምክሮች፡፡

ማጠቃለያ

ምን ተማራችሁ?

- **የተቋማትን እና የኢጋሮችን የጥቃት ጥበቃ አቅም መገምገም/መመዘን ስለሚኖረው ጠቀሜታ ለመረዳት-የጥቃት** ጥበቃ መመዘኛዎችን ከማረጋገጫ መንገዶች ጋር በማዛመድ ስለተቋማት እና ስለኢጋሮች የጥቃት ጥበቃ አቅም ግምገማ አስፈላጊነት ተመልክታችኋል፡፡

- ደህንነቱ **የተጠበቀ የፕሮግራም ቀረጻ ለማከናወን በፕሮግራሙ ዑደት ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ቁልፍ የሆኑ** የጥቃት ጥበቃ ተግባራትን ለመለየት- የጥቃት ጥበቃ ተግባራትን ከፕሮግራም ዑደት ደረጃዎች ጋር አዛምዳችኋል፡፡

- ጠንካራ አመራር እና ተቋማዊ የአሠራር ባህል **ደህንነቱ ወደተጠበቀ አሠራር ለመሸጋገር ያላቸውን አስፈላጊነት ለመገንዘብ-** ከአንድ ፕሮግራም መጀመሪያ አንስቶ በቦታዉ መኖር ያለባቸውን የማረጋገጫ እርምጃዎችን ለይታችኋል፤ እንዲሁም በቦታው ሊኖሩ የሚችሉ የጥቃት ጥበቃ ሥጋቶችን ለይታችኋል፡፡

ራስዎን ለሚቀጥለው ሞጁል ለማዘጋጀት ሊረዷቸው የሚገቡ ነጥቦች፡፡

በሞጁሉ ውስጥ የአህመድን የባህርይ ለወጥ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ኃላፊነት እንደሚሰማው ማኔጀር የሚጠበቁበትን ኃላፊነቶች በአግባቡ መወጣት እንዳይችል አስቸጋሪ/እንቅፋት ሆኖበት የነበረው ምንድን ነው ብለው ያስባሉ?

በዝቅተኛ ደረጃ ወደሚገኙ ኢጋር ተቋማት በሚያደርጉት የመስክ ጉዞ አስቴር ምን አገኛለሁ ብላ ተስፋ ታደርጋለች ብለው ያስባሉ?

በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ ኢጋር ተቋማት እንደ መሪ ኢጋር ተቋም ከኤፍ.ኤፍ.ኤች ምን ሊጠብቁ ይችላሉ?

የጥቃት ጥበቃ ጉዳዮችን በማጠናቀቅዎ እንኳን ደስ አለዎት ሞጁል 2፡-

ከኢጋር ተቋማት ጋር መጀመር!

ኤፍ.ኤፍ.ኤች ባደረገው የመጀመሪያው የጥቃት ጥበቃ እንቅስቃሴ/ዘመቻ አብረው በመሣተፍዎ ደስተኛ ሆነዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

የኤፍ.ኤፍ.ኤች ፕሮጀክት የመስክ ጉብኝት ሲካሄድ በሞጁል 3 የእርስዎን ተሳትፎ በጉጉት እንጠብቃለን። ሁሉም ነገር በታቀደው መንገድ ሊሄድ ይችላል?

የመረጃ እና ድጋፍ ማዕከሉን ጋዜጣ፣ የጥቃት ጥበቃ መረጃዎች፣ ዌብናርስ፣ ፖድካስትስ እና ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን ከመረጃ እና ድጋፍ ማዕከሉ ማግኘት ይችላሉ።

በመቀጠል፣ የትምህርት አፈጻጸም የምስክር ወረቀትዎን ከመረጃና ድጋፍ ማዕከሉ ለማግኘት የሞጁል 2 ግምገማዎትን ያጠናቅቁ፡፡

UKaid
from the British people

የኢትዮጵያ
ማዕከል

መልስ

1.1 ተግባር

✓ የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ ሥልጠና

✓ ቅሬታ የመሰብሰቢያ/የመቀበያ መዝገብ

✓ ጉዳት የማድረስ አደጋ ሥጋት ግምገማ

✓ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ

✓ የጉዳይ (የኬዝ) ምርመራ

✓ የግንዛቤ ማስጨበጫ ቁሳቁሶች

✓ የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ

እዚህ ይጫኑ:: 1.1 ተግባር

1.1 a ተግባር

✓ ከአጋር ተቋማት ጋር በጋራ መሥራት

እዚህ ይጫኑ:: 1.1 a ተግባር

1.2 ተግባር

✓ ሁሉም ፖሊሲዎች ትክክል ናቸው።

እዚህ ይጫኑ:: 1.2 ተግባር

2.1 ተግባር

- ✓ የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ ሥልጠና
- ✓ ቅሬታ የመሰብሰቢያ/የመቀበያ መዝገብ
- ✓ ጉዳት የማድረስ አደጋ ሥጋት ግምገማ
- ✓ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ
- ✓ የጉዳይ (የኬዝ) ምርመራ

- ✓ የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ ሥልጠና
- ✓ ቅሬታ የመሰብሰቢያ/የመቀበያ መዝገብ
- ✓ ጉዳት የማድረስ አደጋ ሥጋት ግምገማ
- ✓ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ
- ✓ የጉዳይ (የኬዝ) ምርመራ

እዚህ ይጫኑ፡፡ 2.1 ተግባር

2.3 ተግባር

- ✓ ተለይተው የታወቁት ስሜቶች በሙሉ ከኃይል አዘል ንግግር ጋር ሊዛመዱ ይችላሉ።

እዚህ ይጫኑ፡፡ 2.3 ተግባር

3.1 ተግባር

✓ የአጋር ድርጅት የድርጅታዊ አቋም ዝርዝር ጥናት ተጠናቋል

✓ ከሁሉም አጋሮች ጋር የተደረጉ ስምምነቶች የጥቃት ጥበቃን የተመለከቱ አንቀጾችን/ድንጋጌዎችን ያካተቱ ናቸው

✓ ሁሉም አጋር ድርጅቶች ደህንነቱ የተጠበቀ የቅጥር ሂደት በስራ ላይ አውለዋል

✓ ከመርሃ ግብር ጋር ሊያያዝ የሚችል የስጋት ግምገማ ተጀምሯል

✓ የቤተሰብ ጤና ፍሮንተር(FHF) የጥቃት ጥበቃ መሪ አለው/ተሰይሟል/ተቋቁሟል

እዚህ ይጫኑ። 3.1 ተግባር

3.3 ተግባር

1. ሪፖርት ያልተደረገ

2. ተገቢውን መልስ የመስጠትና እንክብካቤ የማድረግ ግዴታ

3. መረጃ፣ መገናኛ (ኮሚውኒኬሽን) እና ቴክኖሎጂ

4. ደካማ የሆነ የፕሮግራም ቀረጻ

5. ደህንነቱ የተጠበቀ የቅጥር ምልመላ

6. ችግሮችን ለመፍታት ከአጋሮች ጋር በጋራ መሥራት

እዚህ ይጫኑ። 3.3 ተግባር